## የባንኩ አጭር መረጃ

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በ1935 ዓ.ም. ተቋቋመ፡፡
- በኢትዮጵያ የባንክ አገልግሎትን በማስተዋወቅ እና በማዳረስ ግንባር ቀደም ባንክ ነው፡፡
- በሀገሪቱ እድገት ላይ የማይተካ ሚና በመጫወት ላይ ነው፡፡
- ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች እና አሠራሮች በየጊዜው ተግባራዊ በማድረግ ሁለገብ የባንክ አገልግሎት ይሰጣል፡፡
- የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያማከሉ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡
- እ.ኤ.አ በ2025 ዓለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ንግድ ባንክ ለመሆን በመሥራት ላይ ይገኛል፡፡
- በደቡብ ሱዳን እና ጅቡቲ ቅርንጫፎችን ከፍቷል፡፡
- እ.ኤ.አ እስከ ጁን 30/2019፣
    - 1444 ቅርንጫፎችን በመላ ሀገሪቱ ከፍቷል፤
    - የባንኩ ተቀማጭ ገንዘብ ብር 541.2 ቢሊዮን ደርሷል፤
    - ባንኩ በብድር የሰጠው ገንዘብ 575 ቢሊዮን ብር ደርሷል፤
    - የባንኩ አጠቃላይ ሀብት 712 ቢሊዮን ብር ደርሷል፤
    - ከ38,000 በላይ ቋሚ ሠራተኞች እና ከ22,000 በላይ የኮንትራት ሠራተኞች አሉት፡፡

## ዋና ዋና አገልግሎቶች

1. **የተቀማጭ አገልግሎት**

ይህ አገልግሎት ደንበኞች ገንዘባቸውን ወይም ውድ ንብረቶቻቸውን በባንኩ ማስቀመጥ የሚችሉበት ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፡፡

- **የቁጠባ ሒሳብ አገልግሎት**

የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት ደንበኞች ገንዘባቸውን በባንኩ የሚያስቀምጡበት ነው፡፡ ባንኩ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ፍላጎት ያማከሉ የቁጠባ ሂሳብ አገልግሎት አይነቶች አሉት፡፡

- **ተንቀሳቃሽ ሂሳብ**

ይህ ሂሳብ ወለድ የማይታሰብበት በቼክ የሚንቀሳቀስ አገልግሎት ነው፡፡

- **በጊዜ የተገደበ የተቀማጭ ሂሳብ አገልግሎት**

ይህ የቁጠባ ሂሳብ ደንበኛው ከባንኩ ጋር የሚስማማውን ያክል ጊዜ ገንዘቡን በማስቀመጥ በስምምነት በሚወሰን ከመደበኛው የቁጠባ ሂሳብ ላቅ ያለ የወለድ መጠን የሚታሰብበት አገልግሎት ሲሆን፣ ሂሳቡን ለመክፈት አነስተኛው የገንዘብ መጠን 10,000 ብር ወይም 5,000 ዶላር (በፓውንድ እና ዩሮ አቻ ምንዛሪ) ነው፡፡

- **የውጭ ምንዛሪ ሒሳብ አገልግሎት**

የገቢ ምንጫቸው በውጭ ምንዛሪ የሆኑ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ ዜጎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎችና የመሳሰሉት በአሜሪካን ዶላር፣ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በዩሮ የሚከፍቱት ሂሳብ ነው፡፡

- **የዳያስፖራ ሂሳብ**

አገር ውስጥ ነዋሪ ያልሆኑ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና በእነዚህ ግለሰቦች ባለቤትነት የተያዙ ድርጅቶች በአሜሪካ ዶላር፣ በእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በዩሮ የሚከፍቱት ሂሳብ ነው፡

- **የከበሩ ንብረቶችን የማስቀመጥ አገልግሎት**

ማንኛውም ግለሰብ/ቡድን ውድና የከበሩ ንብረቶቹን ባንኩ ባዘጋጀው ደህንነቱ የተጠበቀ ሳጥን በኪራይ ማስቀመጥ የሚያስችል አገልግሎት ነው፡፡

2. **የብድር አገልግሎት**

ባንኩ ለአገር ውስጥና ለወጪ ንግድ የሥራ ማስኬጂያና ማስፋፊያ፣ እንዲሁም የአጭር ጊዜ፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ብድሮችን ለደንበኞቹ ይሰጣል፡፡

**በባንኩ ከሚሰጡ የብድር አገልግሎቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡**

- ኦቨርድራፍት የብድር አገልግሎት
- ሸቀጥን /ዕቃን/ መያዣ በማድረግ የሚሰጥ ብድር
- በኢትዮጵያ ምርት ገበያ በሚገበያዩ ሸቀጦች መያዣነት የሚሰጥ ብድር
- ለላኪዎች የሚሰጥ የቅድመ ጭነት ብድር
- የሕብረት ሥራ ማህበራት/ዩኒየኖች ለአለም የምግብ ፕሮግራም (WFP) የግብርና ምርት ለማቅረብ ለገቡት ስምምነት የሚሰጥ ብድር

- ለአስመጪዎች በመተማመኛ ሰነድ የሚሰጥ ብድር
- በኤክስፖርት መተማመኛ ሰነድ መያዣነት ላስመጪዎች የሚሰጥ ብድር
- የዋስትና አገልግሎት
- **በተወሰነ ጊዜ የሚከፈል ብድር**

✓ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከወለድ ጋር የሚመለስ ለሥራ ማስኬጃ እና/ወይም ለፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር የሚሰጥበት አገልግሎት ነው፡፡

✓ ባንኩ የአጭር፣ የመካከለኛ እና የረጅም ጊዜ ብድሮችን ይሰጣል፡፡

✓ የአጭር ጊዜ ብድር እስከ 3 ዓመት ድረስ የሚመለስ ነው፡፡

✓ የመካከለኛ ጊዜ ብድር ከ3 እስከ 7 ዓመት ድረስ የሚመለስ ነው፡፡

✓ የረዥም ጊዜ ብድር ከ7 እስከ 15 ዓመት ድረስ የሚመለስ ነው፡፡

**በተወሰነ ጊዜ የሚከፈሉ የብድር አይነቶች**

✓ የተሽከርካሪ መግዣ ብድር

✓ ለላኪዎች ለተሽከርካሪ መግዣ የሚውል ብድር

✓ የግንባታ ማሺነሪዎች መግዣ ብድር

✓ ልዩ የግንባታ ማሺነሪዎች እና የገልባጭ መኪና መግዣ ብድር

✓ ለተለያዩ መሰረተ ልማት ግንባታዎች የሚውል የሥራ ማስኬጃ ብድር

✓ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሠሩ ድርጅቶች የሚሰጥ የኢንቨስትመንት ብድር

✓ ባንኩ ለዕዳ ማካካሻነት የሚሸጣቸውን ንብረቶች መግዣ የሚውል ብድር

✓ ከሌሎች አበዳሪዎች ጋር በጋራ የሚሰጥ ብድር

✓ ለግብርና የሚውል ብድር

✓ ለአነስተኛ የፋይናንስ ተቋማት የሚሰጥ ብድር

✓ በባንኩ ትልልቅ ደንበኞች ዋስትና ሰጪነት የሚሰጥ ብድር

✓ የከተማ አገልግሎቶችን ለማስፋፋት የሚሰጥ ብድር

✓ ለአማካሪ ድርጅቶች የሚሰጥ ብድር

✓ የባንክ ለባንክ ብድር

✓ የምርምር/የፈጠራ ውጤቶችን ለመተግበር የሚሰጥ ብድር

✓ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ ዕቃዎች የመተማመኛ ሰነድ ክፍያ ብድር

✓ከሌሎች ባንኮች የሚገዛ ብድር

✓የቤቶች ልማት ብድር

- **የኮንስዩመር ብድሮች**

የኮንስዩመር ብድር ለግለሰብ ደንበኞች የሚሰጥ ሲሆን ባንኩ የሚከተሉትን የኮንስዩመር ብድር አይነቶች ይሰጣል፡፡

✓ የኮንዶሚኒየም ብድር
✓ ለኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች የቤት መግዣ/መሥሪያ ብድር
✓ በዓለማቀፍ ድርጅቶችና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያድ) ለሚሠሩ ሠራተኞች የሚሰጡ
  - ለግል ጉዳይ የሚውል ብድር
  - የአውቶሞቢል መግዣ ብድር
  - ለመኖሪያ ቤት መግዣ/መሥሪያ የሚሰጥ ብድር ናቸው፡፡

**3. የዓለም አቀፍ ንግድ አገልግሎት**

ባንኩ ደንበኞች የሚሠሩትን ዓለም አቀፍ የገቢና ወጪ ንግድ ለማሳለጥ የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

- የመተማመኛ ሰነድ
- ሰነዶችን ለክፍያ መላክ
- ቅድሚያ ክፍያ
- ያለ ቅድሚያ ክፍያ ወይም ዋስትና ዕቃን ለሽያጭ ለወኪል መላክ
- የዋስትና ሰነድ
  ✓ የጨረታ መሳተፊያ ዋስትና፣
  ✓ የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና፣
  ✓ የቅድሚያ ክፍያ ዋስትና፣
  ✓ የብድር ዋስትና፣
  ✓ የቀሪ ክፍያ ዋስትና እና
  ✓ ለቀረጥ ተከፋይነት የሚሰጥ የዋስትና ሰነድ
- ያለውጭ ምንዛሪ ክፍያ ለሚገባ ዕቃ የሚሰጥ ፈቃድ
- ወደ ውጭ የሚላኩ አነስተኛ ዕቃዎች ፈቃድ

## 4. ገንዘብ ማስተላለፍ እና የውጭ ምንዛሪ ግዢ አገልግሎቶች

- የሀገር ውስጥ ሐዋላ
- የውጭ ሀገር ሐዋላ
- የስዊፍት አገልግሎት
- የውጭ ምንዛሪ ግዢ

**ባንካችን ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን የተለያዩ የውጭ ሀገራት ጥሬ ገንዘቦች ይገዛል፡-**

- ✓ የአሜሪካን ዶላር
- ✓ የእንግሊዝ ፓውንድ
- ✓ ዩሮ
- ✓ የስዊዝ ፍራንክ
- ✓ የስዊዲን ክሮነር
- ✓ የኖርወይ ክሮነር
- ✓ የዴንማርክ ክሮነር
- ✓ የጃፖን ዬን
- ✓ የካናዳ ዶላር
- ✓ የሳውዲ ሪያል
- ✓ የተባበሩት አረብ ኤመሬቶች ድርሀም
- ✓ የማዕከላዊ አፍሪካ ፍራንክ

ከላይ ከተዘረዘሩት የውጭ ሀገር ገንዘቦች በተጨማሪም ባንኩ ከታች የተዘረዘሩትን የውጭ ሀገር ገንዘቦች ለገቢ እና ወጪ ንግዶች እንዲሁም ከውጭ ለሚላክ ገንዘብ አገልግሎት ከሂሳብ ወደ ሂሳብ ለማስተላለፍ ይገለገልባቸዋል፡-

- ✓ የአውስትራሊያ ዶላር
- ✓ የቻይና ዩዋን
- ✓ የህንድ ሩፒ
- ✓ የደቡብ አፍሪካ ራንድ

## 4. ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎት

የሸርዓ የፋይናንስ መርሆችን በመከተል ምንም አይነት ወለድ መክፈልም ሆነ መቀበል ላይ ያልተመሠረተና በተፈቀዱ ሥራዎች ላይ ብቻ የሚሳተፍ የራሱ የሆነ አሠራር የሚከተል አገልግሎት ነው፡፡ ባንኩ የሚከተሉትን ከወለድ ነፃ የባንክ አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

- የተቀማጭ ሂሳብ አገልግሎት

- የፋይናንሲንግ /የንግድ ሥራ አጋርነት/ አገልግሎት
- የዋስትና አገልግሎት
- የዓለም አቀፍ ንግድ ድጋፍ አገልግሎት
- የገንዘብ ማስተላለፍ /ሐዋላ
- የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ አገልግሎት

## 5. የኤሌክትሮኒክ ክፍያ አገልግሎት

ባንካችን የኤሌክትሮኒክስ መሣሪያዎችን በመጠቀም የሚከተሉትን አገልግሎቶች ይሰጣል፡፡

- ሲቢኢ ብር
  - ✓ ገንዘብ መላክ፣
  - ✓ ገንዘብ ማውጣት፣
  - ✓ የስልክ የአየር ጊዜ መሙላት፣
  - ✓ የክፍያ አገልግሎት መፈጸም፣
  - ✓ ቀሪ ሂሳብ ማወቅ፣
  - ✓ ሌሎችም።

- የኤቲኤም አገልግሎት
- የውጭ ምንዛሪ ኤቲኤም
- የሞባይል ባንክ አገልግሎት
- የኢንተርኔት ባንክ አገልግሎት
- በካርድ ክፍያ መፈፀሚያ ማሽን (POS) አገልግሎት


**የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ**
**Commercial Bank of Ethiopia**

አድራሻ : ጋምቢያ ጎዳና
ፖ.ሣ.ቁ 255

ስልክ +251-11-551-50-04/122-87-55

ፋክስ +251-11-122-89-66

የስዊፍት አድራሻ ፡- CBETETAA

የደንበኞች ግንኙነት ማዕከል ፡- 951

ኢሜይል፡ cbecommun@combanketh.com

ድረ ገጽ፡ www.combanketh.com

Facebook: www.facebook.com/combanketh

https://www.twitter.com/combanketh

www.linkedin.com/company/commercialbankofethiopia

www.youtube.com/commercialbankofethiopia

Telegram: https://t.me/combankethofficial